# እግዚአብሔርን ታመን

እንዲህ ይነበባል፡

በገለዓድ ቴስቢ የነበረው ቴስብያዊው ኤልያስ... አክዓብን በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው።

የጌታም ቃል እንዲህ ሲል ለእርሱ መጣለት።

ከዚህ ተነሥተህ ወደ ምሥራቅ ሂድ፥ (ማለት የፈለግኩት) በዮርዳኖስም ትይዩ ባለው በኮራት-በኮራት ፈፋ ውስጥ ተሸሸግ።

ከወንዙም ትጠጣለህ፥ ቍራዎችም በዚያ ይመግቡህ ዘንድ አዝዣለሁ...

ሄደም እንደ ጌታ ቃልም አደረገ። ሄዶም በዮርዳኖስ ትይዩ ባለው በኮራት ፈፋ ውስጥ ተቀመጠ።

ቍራዎቹም በየጥዋቱ እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር፤ በየማታውም እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር፤ ከወንዙም ይጠጣ ነበር።

ከብዙ ቀንም በኋላ በምድር ላይ ዝናብ አልነበረምና ወንዙ ደረቀ።

ተነሥተህም በሲዶና አጠገብ ወዳለችው ወደ ሰራፕታ ሂድ፥ በዚያም ተቀመጥ፤

እነሆም፥ ትመግብህ ዘንድ አንዲት ባልቴት አዝዣለሁ የሚል የጌታ ቃል መጣለት።

ተነሥቶም ወደ ሰራፕታ ሄደ፤ ወደ ከተማይቱም በር በደረሰ ጊዜ አንዲት ባልቴት በዚያ እንጨት ትለቅም ነበር፤ እርሱም ጠርቶ። የምጠጣው ጥቂት ውኃ በጽዋ ታመጭልኝ ዘንድ እለምንሻለሁ አላት።

ውኃም ልታመጣለት በሄደች ጊዜ ወደ እርስዋ ጠርቶ፥ ቁራሽ እንጀራ በእጅሽ ይዘሽ ትመጪ ዘንድ እለምንሻለሁ አላት። እርስዋም።

አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን! በማድጋ ካለው ከእፍኝ ዱቄት፥ በማሰሮም ካለው ከጥቂት ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም፤ እነሆም፥ ገብቼ ለእኔና ለልጄ እጋግረው ዘንድ በልተነውም እንሞት ዘንድ ጥቂት እንጨት እሰበስባለሁ አለች።

ኤልያስም አላት። አትፍሪ፤ ይልቅስ ሄደሽ እንዳልሺው አድርጊ፤ አስቀድመሽ ግን ከዱቄቱ ለእኔ ታናሽ እንጎቻ አድርገሽ አምጭልኝ፥ ከዚያም በኋላ ለአንቺና ለልጅሽ አድርጊ።

**ጌታ የእስራኤል አምላክ እንዲህ ይላልና። በምድር ላይ ጌታ ዝናብ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ፥ ዱቄቱ ከማድጋ አይጨረስም፥ ዘይቱም ከማሰሮው አይጎድልም።**

**እርሰዋም ሄዳ እንደ ኤልያሳ ቃል አደረገች፤ እርሰዋና እርሱ ቤትዋም ብዙ ቀን በሉ።**

**በኤልያሰም እጅ እንደ ተናገረው እንደ ጌታ ቃል ዱቄቱ ከማድጋው አልተጨረሰም፥ ዘይቱም ከማሰሮው አልጎደለም።**

ወደ ጠለቀው ከመግባታችን በፊት፣ ለማለዳው ንግግር፥ እግዚአብሔርን ታመን፡ የሚለውን ርእስ መርጫለሁ።

2 አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ቃልህ ሲሰበክ ባርክልን፥ እንዲሁም መንፈሰ ቅዱሰ፥ እንዲመጣልን እንደጠየቅነው፥ ልባችን እና ሐሳባችንን እየተቆጣጠረ ለጉብኝቱ ያዘጋጀን ዘንድ፥ ይምጣ። ሰለ አንተ እንድናውቅ፥ ባህሪህን፣ መንገድህን እና ምክንያትህን አውቀን፥ በእግዚአብሔር ታምነን፥ ከእውነተኛ ማረጋገጫ ጋር የሕይወትን ውጣ ውረዶችን መጋፈጥ እንድንችል እንጂ፥ ለመታየት እና ለማየት ወደ ጌታ ቤት አንመጣምና። በኢየሱስ ሰም እንጸልያለን። ይሁን ጌታ ሆይ። አሜን።

3 አሰፈሪ ማለዳ የነበረ ይመሰላል። በጣም ሃሩር እና አቧራ ሆኖ፥ ሰዎች ተርበው፥ በየመንገዱ ወድያ ወዲህ እያሉ፥ ምድር ለመንደድ ቀርባለች። ይህ ሁሉ፥ የሐጢአታቸው እና የሰብእናቸው መውደቅ ውጤት ነበረ።

4 አያችሁ፥ በዘመኑ፥ አክዓብ በእሰራኤል ላይ-በእሰራኤል ላይ ነግሶ ነበር፥ ከእሰራኤል ነገሰታቶች ሁሉ ይልቅ ግን፥ ክፉ ነበር። እንደ አክዓብ ያለ ክፉ ንጉሰ አልነበረም፥ መልካምን አውቆ ትምህርትን ቀምሶ ሳለ፥ በሰራው ሁሉ እግዚአብሔርን ማሳዘኑ መተው አልቻለም። ምንም እንኳ በእርሱ በዘመን፥ ከመንግሰቱ በታች ያለ ህዝብ ሁሉ በልጽጎ የነበረ ቢሆንም፥ እንዲሁም ታላቅ ወታደራዊ ሰልት የነበረው ቢሆንም፥ እግዚአብሔርን አሰቆጥተህ ብዙ ርቀት እጓዛለሁ ማለት የማይጠበቅ ነው።

5 በተጨማሪ፥ በጋብቻው፥ ከወገኖቹ መካከል ከማግባት ይልቅ፥ ወደ ሌላ ሄዶ፣ ጣኦት አምላኪ፣ ለጣኦት የምትሰግድ፥ ሐጢአተኛን አገባ። ኤልዛቤልን አገባ። አማኝ አልነበረችም።

6 ምንም ቢሆን፥ አማኝ የማያምን ማግባት የለበትም። ሁሌም አማኞችን ማግባት አለባችሁ።

7 አክዓብ ግን ይህን ክፋት አደረገ። በእርግጥ ኤልዛቤል ያለጥርጥር ውብ ሴት ነበረች። ማንነቷን ከማየት ይልቅ ግን፥ መልኳን አይቶ ወደቀላት። ይሄው እሰከ ዛሬም ድረሰ፥ ብዙ ሰዎች ተመሳሳይ ሰሕተት እየፈጸሙ ይገኛሉ።

8 በአገሪቱ ላይ፥ በህዝቡ መካከል የጣኦትን አምልኮ አመጣች። ህዝቡ እና ካህናቱ፥ አገልጋዮቻቸውም ሁሉ፥ ለዝነኛው ታልቅ መሰሕብ ወደቁ።

9 ይህ ነገር፥ ዛሬ የአገራችን ትክክልኛ ምሰል ነው። ከዝነኛ መሰሕብ ሰር ወድቀናል። መንግሰት ብቻ ይፍቀድ እንጂ፥ ካህናት፥ ችግር እንደሌለው ማሰባቸው አያጠራጥርም። እኔ ግን መንግሰት ቢፈቅድ ባይፈቅድ አይገደኝም፥

ዋናው ነገር እግዚአብሔር መፍቀዱ ነው። ሰዎቹ ሁሉ፥ በተወሰነ መልኩ ዓለማዊ ነገሮቻቸው ላይ ቢሳተፉ ችግር የሌለው መሰላቸው።

10 ምናልባትም አንድ ሰው የዛሬ ትክክለኛ ምስሏ ነው ባልኩት ነገር ላይ፥ ላብራራለት የሚጠይቅ ይኖር ይሆናል። ጣኦት አምላኪዎች ነን ብለን ላናስብ እንችላለን፥ ቢሆንም ነን። መንግስትም ይደግፈዋል። ዛሬ ዛሬ ሰዎች ጣኦት አምላኪዎች ስለሆኑ-ስለሆኑ፥ ጣኦትን ያመልካሉ። አንዳንዶቻቸው፥ ገንዘብን እንደ ጣኦት ያመልካሉ። ሌሎችም፥ የቴሌቪዥን አክተሮችን፥ እንደ ጣኦት ያመልካሉ። ምንም ይሁን ምን፥ ከእግዚአብሔር በፊት የምታሰቀድሙት የትኛውም ነገር፥ ጣኦት ነው።

11 ታላቁ ጠላታችን፥ ሰይጣን፥ አንዳንዴ፥ ቤተክርስትያንን ከእግዚአብሔር በላይ አድርጎ በማሳየት፥ የተካነ ነው። ቤተክርስትያናችሁ ታላቅ ሊሆን ይችላል። የሚያስደንቅ ሕንጻ ሊሆን ይችላል፥ ወይም ታላቅ የሐይማኖት ተቋምም ይሁን። ታላቅ ጉባኤም ሊሆን ይችላል፥ በልባችሁ ግን፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ የምታሰቀድሙት ምንም ነገር አይምጣ። ከእግዚአብሔር በላይ የሆነ ነገር ሁሉ፥ ጣኦት ነውና።

12 እነዚህ ህዝቦች እንደ ድሮ በሌሎች መንግስታት ዘመን እንደነበሩበት ዓይነት ፡ መንፈሳዊ እንዳልነበሩ አውቀው ነበር። ሐይማኖተኛ አገር በመሆናቸው ግን ፡ ሁሉ ነገር ፡ መልካም ይሆናል ብለው አሰቡ። እኛ ወደዚህ ሁኔታ የመጣንበት መንገድም ይህንኑ ነው።

13 ከጥቂት ወራት በፊት ከአንድ መልካም ወዳጄ ጋር እየተጫወትኩ ነበር። እንዲህ አለኝ፦ "ወንድም ብራንሀም፥ ይህች ዩናይትድ ስቴትስን እጅግ የዘቀዘቅካት ይመስለኛል።" "ሁሌ ስለ ሐጢአትዋ እና እግዚአብሔር ምድሪቱ እንዴት እንደሚቀጣት ብቻ ትጮሀለህ፡ አለኝ።"

14 እኔም፦ "ጻዲቅ ይሆን ዘንድ፥ ይህንን ማድረግ አለበት አልኩት።"

እርሱም አለ፦ "ግን'ኮ፥ ወንድም ብራንሀም፥ ይህች አገር በጌታ ቃል መሰረት እንደ ተመሰረተች ረስተሀል። አባቶቻችን ወደዚህ መጡ፥ እግዚአብሔርም ርስት አድርጎ ሰጠን። የሀይማኖት አገር ነን።"

15 እኔም አልኩት፦ "ሁሉ፥ እውነት ነው። ይህችን አገር እንዴት እንደማደንቃት ማንም አያውቅም! ነገር ግን፥ ወንድሜ፥ አስተውል፥ እስራኤልም፥ ነብያቶቿንና የከበሩ ሰዎች የተላከላት በእግዚአብሔር የተመረጠች አገር ነበረች። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሐጢያትን አይታገስም። እስራኤላውያን የዘሯትን ሰብል ሁሉ እንዲያጭዱ አድርጓቸዋል። እስራኤል የዘራችውን እንድታጭድ ከአደረገ፥ የዘራነውን እንድናጭድ ያደርጋል። እርሱ የሰጋ ለባሽ አክባሪ አይደለምና።"

16 አባቶቻችን ባደረጉት ነገር ላይ፥ የታላላቅ አብያተ ክርስትያናት መስራቾች፥ ለእግዚአብሔር ባደረጉት ታላቅ መስዋእትነት ስለተደገፍን፥ እረፍታችን እንዲሁ ባለው ሁኔታ እንደሆነ አሰበናል፥ መልካም እና በጣም የሚደነቅ ነገር ቢሆንም፥ መዳናችን እነርሱ ከሰሩት ስራ መምዘዝ አንችልም! መዳን በእግዚአብሔር እና በግለሰብ መካከል የሚደረግ የግል ጉዳይ ነው። ከአገራችን ጋር፣ ከቤተክርስትያን ጋር ሳይሆን፥ በጌታ ፊት፥ እኛው መልስ እንሰጣለን።

17 በአገራችን ውስጥ፥ አሉን በምንላቸው መንፈሳዊ ሰዎች መሀል ሳይቀር፥ መንፈሳዊ ወደ ሆነ ወንድም ወይም እህት ስትሄዱ፥ ልቦቻቸው ውስጥ አንዳች ነገር ወደ መጉደል ደርሰዋል።

18 ባለፉት ጥቂት ሳምንታት፥ እንዲህ ባሉ ጉዳዮችንን ስጠቃቅስ ስንብቻለሁ፥ ቁምነገረኞች ብየ ሳሰባቸው በነበሩ ሰዎች ያንን ስፈልግ ነበር፥ ነገር ግን ወዲያና ወዲህ እየተፍገመገሙ፥ አትኩሮታቸው ሁሉ፥ ጊዜአዊ በሆኑ ነገሮች ላይ አድርገው አገኘኋቸው። "እግዚአብሔር ትልቅ ነገር ሰጠኝ **ይሄን-እና-ያንን** ሰጠኝ። እግዚአብሔር... ሰጠኝ" ግብዞች ሆናቿል።

19 ታላላቅ ቁሶች አብዛኛው ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ አይውሉም። እግዚአብሔር'ኮ በጻዲቁም፣ በሐጢያተኛውም ላይ ያዘንባል። ዛሬ ዓለም የሚያስፈልጋት፥ እራስህን እንደሆነ ነገር አድርገህ የምትገበዝበት እና መንፈሳዊ ብለህ የምትጠራው የእምነት መገበዝ አይደለም።

20 አንዳንዴ፥ መንፈሳዊ ልብ ሳይኖር፥ እምነት ብቻ ታላላቅ ተአምራቶችን ያደርጋል። ጌታችንስ፦ "በዚያች ቀን ብዙዎች ወደ እኔ ይመጣሉ፥ 'በስምህስ፥ ይህን ያን አላደረግንምን? ' ይሉኛል፥ እኔም፥ 'እናንተ አመጸኞች ከእኔ ራቁ' እላቸዋለሁ።" ብሎ የለምን። አመጽስ ምንድነው? መልካምን ለማድረግ አውቃችሁ ነገር ግን አለማድረግ እኮ ነው። "በጭራሽ አላውቃችሁም" ይላቸዋል። እኛም በዚያች ዘመን እየኖርን እንገኛለን።

21 ዛሬ የሚያስፈልገን የቁስ ብዛት አይደለም። ያ እማ አለን። ታላላቅ አብያተ ክርስትያናት አያሻንም። ታላላቅ ጉባኤዎች አይደለም የሚያስፈልገን። ተጨማሪ ሬድዮ እና ቴሌቪዥን አያስፈልገንም። ተጨማሪ ነገሮች አያስፈልጉንም። ነገር ግን፥ ዛሬ መንፈሳዊ ለመሆን የሚያስፈልገን፥ በእግዚአብሔር ፊት እራሳቸውን ትሁታን የሚያደርጉ ሰዎችና፥ ሰባራ ሳንቲም ባይኖራቸው፥ በእነርሱ ውስጥ ያለው መንፈስ፥ በጌታ መልካምነት እስኪረካ ድረስ የሚጸልዩ፥ በልባቸው ውስጥ ሪቫይቫል የሚሆንላቸው፥ ባህርያቸው እና የሚኖሩበት ሁኔታን መቀየር የሚችሉ ሰዎች ያስፈልጉናል።

22 ለእግርህ የምትቀይረው ጫማ ላይኖርህ ይችላል፥ የነተበ ልብስ ለብስህ ሊሆንም ይችላል፥ በልብህ ግን የጌታ ዜማ የሚዘምር የሆነ ነገር አለህ። እኔም በዓለም ከአለው ሀብት ሁሉ ይልቅ ይህንኑ ቢኖረኝ እመርጣለሁ።

23 ስለዚ ስጋዊ ነገሮች ሁሌም የእግዚአብሔር በረከት ምሳሌዎች ናቸው ማለት አትችሉም። ዳዊት፦ ሐጥአን እንደ ሊባኖስ ዝግባ... ከፍ ከፍ ሲሉ እንዳየ፥ ወደ ጌታ ይናገራል። እግዚአብሔር ግን "ፍጻሜውን አስተዋልከውን? " ብሎ ጠየቀው፥ ምንም ያህል መልካም ልብስ ብንለብስ፥ ምንም ያህል ምግብ ብንመገብ፥ ወደ እግዚአብሔር መገኘት የሚሄድ እርሱ አይደለም። ይህ አሁን ያደርንበት ስጋ፥ ምንም ያህል ብትጠነቀቁለት፥ ጠፊ ነው። በሰው ውስጥ ያለች ነፍስ ግን ትገባለች፥ ወደ ህያው እግዚአብሔር መገኘት የሚገባ የመንፈስ አቋም ነው።

24 ነገሮች ሁሉ ያው እንደሆኑ አርገን እናስባለን። ህዝብ ስለሆንን ብቻ ያን እናስባለን... አክዓብና እስራኤል ሁሉ፥ በዚያ ቀን፥ ነገሮችን ያው አርገው ቆጠሩ፥ ችግር እንደሌለ አሰቡ። ካህናቶቻቸው እና ሰባኪዎቻቸው፦ "መልካም ነው። ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ሊሏቸው ሞከሩ።" ክፋትን በመቃወም፥ ድምጹን ከፍ

አድርጎ ያወጀ አንድ ሰው ግን ነበረ፥ ቅዱስ እግዚአብሄር በዘመናዊና ባልተቀደሱ የሐይማኖት ዝንባሌዎች ደስ እንደማይሰኝ አውቆ ነበርና።

25 የሰማይ አምላክ ግን ዛሬም ያው ሆኖ ይኖራል። በፊቱ በሙላት ከተቀደሰ ህይወታችን ውጪ፥ ልንሰራቸው በምንሞክራቸው ታላላቅ ነገሮች እና ጥረቶቻችን በፍጹም ደስ አይሰኝም።

26 ትምህርት ቤቶችን፣ ሙኩራቦችን እና ቅዱሳን ቦታዎችን ልንገነባ እንችላለን። ተቋም ሊኖረን ይችላል። የሰው ነፍስ በጌታ መሰውያ ስር ተቀድሳ፥ ለእግዚአብሔር ሰራ የተሰጠች እስካልሆነች ድረስ ግን፥ ታላላቅ ነገሮች ብናደርግም፥ ጌታን ደስ አያሰኘውም። አሁን አሁን እንዲህ ዓይነቱ አታገኙም።

27 የጸሎት ጉባኤዎቻችን እጅግ ደካማ ሆኖአል፥ ከአንድ ደቂቃ ጸሎት በኋላ፥ አልጋ ላይ እንሰቀላለን። በቀን አንድ ወይም ሁለቴ። ያም ደግሞ፥ ሁላችንም ጥፋተኞች ነን። አገራችን፥ በሞራል፥ እየበሰበሰች ትገኛለች። ቢሊ ግራሀም እና ኦራል ሮበርትስ በየሰፍራው አሉ። ቢሆንም በአሜሪካ ልብ ውስጥ፥ ዳግም ወደ ህያው አምላክ፥ ወደ ህያው ልምምድ፥ በህያው አምላክ ላይ ወደ አለው ወደማይሞተው እምነት ለመመለስ፥ አሁንም ጥማት አለ፥ እንደው፥ ውጣ ለማለት ይመስል፥ አእምሯችን መደብደብ ብቻ ነው።

28 ደረታችን ወጥቶ፥ ኮሌታችን ወደ ኋላ አዙረን፥ በየመንገዱ "ክቡር" "ዶክተር" ለመባል፥ እንዞር ይሆናል። በምድሪቱ አለ የሚባለውን የትልቁ ቤተክርስትያን እረኛ ልንሆንም እንችል ይሆናል፣ በኑሯችን ማንም ሰው ጣቱን ሊቀሰርብን የማይችል፥ መሆን ከምንችለው በላይ ሃይማኖተኛ ሰው ብንሆንም። በእኛ ውስጥ ያለችውን ነፍስ፥ እሱን የሚናፍቅ ነገር ኖሯት፥ ሰለ ጌታ ቀናተኛ እስካልሆነች ድረስ! "ዋላ ወደ ውሀ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ ጌታ ሆይ፥ ነፍሴ አንተን ተጠማች።" ወደሚል ልምምድ እስካልገባን ድረስ!

29 ስለዚህ፥ እነኮሙኒዝም፥ እና ሌሎች፥ እንደለመዱት ሜዳውን ይጠቀሙበታል፥ የምናደርጋቸው ሰብሰባዎች ሁሉ ሊያስቆማቸው አይችልም። ይህ እንደሚመጣም አስቀድሞ ትንቢት ተነግሯልና። እግዚአብሔር ግን ቤተክርስትያኑን እየተጣራት ይገኛል።

30 ያች የኤልያስ ባለሞያ፥ እንዴት ያለች ሴት ነበረች! ብዙዉን ጊዜ ሰራችሁ ምንነታችሁ ያሳያል። አስታውሱ፥ አሕዛብ ነበረች፥ አይሁድ አልነበረችም። በተጨማሪም፥ የእግዚአብሔር ነብዩ ለመንከባከብ ተመርጣ ነበር።

31 ምድሪቱ ግላለች። ሴቲቱም፥ በባልቴትነትዋ፥ የአማኝ ምሳሌ መሆንዋ… እንደምናየው : የእግዚአብሔር ነብዩ መንከባከብ የምትችልበት ብቃት ባይኖራት ኖሮ፥ ጌታ አይጠራትም ነበር። የገዛ ነብዩንም ወዳልተገባ ቤት ባልላከው ነበር።

32 የነብዩው ምርጫው አልነበረም። የእግዚአብሔር ምርጫ እንጂ። የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንጂ። የእርሷ ትእዛዝ አልነበረም። በፈፋው ተቀመጥ ተባለ። ቁራዎችም ይመግቡት ነበር። አንዲት ነገር ይሆን ዘንድ ግን የእግዚአብሄር ትእዛዝ ነበር። እግዚአብሔርም በእምነትዋ ከኤልያስ ባህርይ ጋር አንድ ወደ ነበረች ወረደ።

33 ሴቲቱ መበለት ነበረች። ባልዋ የሞተባት፣ ልጅ የምታሳድግ መበለት፥ በምን ዓይነት ሁኔታ ልታልፍ እንደምትችል ሁላችንም እንረዳዋለን።

34 በምድሪቱ ላይ፥ የሰብላቸው ጥገኞች ናቸው። ዛሬ እንዳለን አይነት ፕሮጀክቶች፥ እና - እና መጠባበቂያ ተክሎች የላቸውም ነበር። የእርሻቸው ጥገኞች ነበሩ። በህዝቡ አመጽ እና የሰነምግባር መበላሸት፥ ምድሪቱ ላይ ድርቅን አመጡ፥ በዚህም፥ ይራቡ እና ይሞቱ ነበር።

35 ስለዚህም በማድጋ የነበረው ምግብ እየወረደ፥ እየወረደ፥ እየወረደ ማየት በጀመረች ጊዜ፥ ሌሊቱን ሙሉ፥ ከሌሊት ወደ ሌሊት መጸለይዋን ያለጥርጥር እንመለከታለን። የነበራት እፍኝ ዱቄት ብቻ ነበርና። እፍኝ ዱቄት በጭራሽ ወደ ሌለበት ሁኔታ ውስጥ መግባት ግድ ነበር። በቤትዋ ደጅ፥ ሞት በቀጥታ ወደ በሯ እየተንደረደረ ነበር። ምድር ሁሉ ተርባለች። ሌላ የምታገኝበት መንገድ በፍጹም አይታሰብም።

36 በማሰሮ ውስጥ የቀረው ዘይትም አንድ ማንኪያ ብቻ ናት። በእሷ እና በሞት መካከል፥ የዘይቱ እና የዱቄቱ ያህል ርቀት ቀርቶ ነበር። ጸሎቷ በትክክል ከልብ የመነጨ ሳይሆን አይቀርም። እስኪ የእናንተን ቤት ቢነካና፥ ሞት በደጅ መቆሙን ስታውቁ፥ ከማለዳው ይልቅ አብዝተን ከልባችን እንሆን ነበር።

37 ምናልባት ሌሊቱን ሙሉ፥ ይህን ያህል ሰለጸለየች፥ በቀጣዩ ቀን ነገር ተስተካከለላት፥ ብለን እናሰባለን፥ ብየ አምናለሁ። ሶስት ወይም አራት አመት የሆነውን የህጻን ልጅዋን የገረጣ ከንፈር እያየች። የሰውነቷ ስጋ ከአጥንቶቿ ሲረግ፥ አጥንቶቿ እየመነመነ ሲሄድ ታያለች። ይህች እናት፥ ነገሮች እንዲህ ሲሆኑ እያየች ስትሄድ፥ እጅግ አስከፊ ነገር ሳይሆን አይቀርም። በዚህ ሁሉ፥ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርጋ እየጸለየች፦ “አሁን ወደ እፍኝ ዱቄት እና አንድ ማንኪያ ዘይት ብቻ ወርደናል” እያለች፥ ቀን እና ሌሊት፥ ትጸልያለች።

38 ታውቃላችሁ፥ እንግዳ ነገር ነው። ዳግም ስሰብክ ባትሰሙኝ፥ ይህን ነገር ጌታ በሁላችሁ ላይ ያኑር። ይህ ነገር መልእክት ይሁንላችሁ። እንግዳ ነገር ነው፥ አንዳንዴ ጌታ በዚህ መልኩ ይሰራልና፥ እጅግ እንግዳ ነገር ነው።

39 ታውቃላችሁ፥ ሐጢአቶቻችን ስንናዘዝ እና እግዚአብሔር ልናሟላው የሚጠብቀን ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ አሟልተን... በእግዚአብሔር ሰናምን። እንደ ፈቃዱ፥ መሰማማት ያለባቸው ሁኔታዎች ይኖራሉ። ሐጢአቶቻችን እና የሰራናቸው ስሕተቶች ተናዝዘን ሳለን፥ ማድረግ በሚቻለን መልኩ፥ ትክክል አድርገን። እግዚአብሔር አምላክ የጠየቃቸውንና፥ ያዘጋጃቸውን፥ ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ አሟልተን ሳለን፥ ዝም ይለናል። በቃ አይመልሰልንም።

40 በዚህ ማለዳ፥ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ለደረሱ ሰዎች እየተናገርኩ እንደሆነ፥ እርግጠኛ ነኝ። እኔም፥ ብዙ ጊዜ፥ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ገብቼ አውቃለሁ። መለስ ብየ፥ እያንዳንዷ ድንጋይ እየገለጥኩ ያለፈውን ህይወቴ ስመረምር፥ የተሳሳትኩትን ነገር ካገኘሁ፥ ተነስቼ እናዘዝና፦ “ጌታ አምላክ ሆይ፥ እታረማለሁ፥” እላለሁ፥ ሄጄም እፈጽመዋለሁ። ከዛ በኋላ እመጣና፦ “ጌታ ሆይ፥ አንተ አምላክ ነህ፥ ትመልሰልኛለህ። አድርግ ያልከኝን ቅድመ ሁኔታዎችን ሁሉ በርግጥ ፈጽሜያለሁና። ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ፥ አሟልቼአለሁ እለዋለሁ።” ይሁን እንጂ ምንም አይንቀሳቀስም፥ ዝምታ የበዛ ይመስላል፥ አምላክ መሆኑን መታመን ያለባችሁ ያኔ ነው። ተስፋ አትቁረጡ። ማድረግ ያለባችሁ፥ ብቸኛው ነገር፥ በልባችሁ ውስጥ፥ እግዚአብሔርን መታመን ነው።

41 የእኔ ርዕሰ። ምንም ነገር ከማድረጋችሁ በፊት፥ እርግጠኞች ሁኑ። እርሱ አምላክ እንደሆነ ፡ በልባችሁ ውስጥ፥ ታመኑት። ከዛ በኋላ የተናገራቸውን ተፈጽመው ሰታዩ፥ አምላክ መሆኑን እርግጠኛ ትሆናላችሁ፥ እምነት መሰራት የሚጀምረውም፥ ያኔ ነው። እርሱ አምላክ መሆኑን ስለሚያውቅ፥ እምነት ጸንቶ ይቆማል።

42 እርሱ እንደሆነ አምናችሁት፥ እምነት ጸንቶ ቁሟል። ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ አሟልታቿል። ኦ፥ ሰሙ ይባረክ! እምነት፥ ተግተው ለሚሹት እግዚአብሔር የሚሸልም መሆኑን ስለተረዳ፥ አይነቃነቅም።

43 እናንተ የብራንሀም ተበርናክል፥ ይህ ነገር በጥልቀት ወደ እናንተ ይግባና አይወሰድባችሁ። አምላክ የሚጠይቃቸው ቅድመ ሁኔታዎች ካሟላችሁ፥ እግዚአብሔር እምነትን መፈተሽ ስለሚወድ፥ እምነታችሁን እየፈተነ እንዳለና፥ አምላክ እንደሆነ በልባችሁ ከታመናችሁት። ሐጢአቶቻችሁ ተናዛችሁ፥ ጌታ የሚፈልጋቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ አሟልታችሁ ሳላችሁ፥ አሁንም ዝም ካለ፥ እምነት እርሱ ነው እንደሚል፥ አትርሱ። ከዛ በኋላ እምነት ይህ ሁሉ ምን እንደሆነ ሳያውቅ፥ እርሱ እንደሆነና፥ በርግጥ እርሱ እንደሆነ አውቆ፥ በእርሱ ዘንድ ይጸናል።

44 ሰለዚ አስታውሱ፥ እርሱ ከሆነ፥ ቃሉ እውነት መሆን ይኖርበታል። እንዲሁም በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች እንድታልፉ ከፈለጋችሁ፥ እናንተም ከፈጸማችሁት፥ ቃሉን የማክበር ግዴታ ይኖርበታል። ወደ ኋላችሁ ተመልሳችሁም ግን "... እንደው፥ እኔ፥ ተፈውሼም አላውቅ" አትበሉ። አንተ ምስኪን ሰው፥ ኦ እምነቱ የደከመ። ይህንን አትመን። ሁሉንም ነገር ከወጣልህና፥ ተናዘህ ከሆነ፥ የጌታን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተህ ከሆነ፥ እምነት ያኔ ይጸናል። የሚያወዛውዘው ምንም ነገር አይኖርም። አምላክ ነው፥ አንተም እርግጠኛ ነህ። "ጌታን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ሀይላቸውን ያድሳሉ፥ እንደ ንሰር በክንፍ ይወጣሉ። ይሮጣሉ አይታክቱም፥ ይሄዳሉ አይደክሙም።"

45 ቆይ፥ ቅድመ ሁኔታው ካሟላህ። እምነትህ ወደ ተግባር ያደርሰልሃል። የአምላክን ቅድመ ሁኔታ... ካሟላህ፥ ካደረጋችሁ፥ ወይም ከፈጸማችሁ፥ ሙሉ ለሙሉ ካሰባችሁበት፥ እግዚአብሔር እንድታደርጓቸው የሚጠብቃችሁ ነገሮች ሁሉ አድርጋችሁ ከፈጸማችሁ፥ አምላክ እንደሆነ፥ እምነታችሁ ይጸናል። በእግዚአብሄር የታመናችሁ ሁኑ።

46 ታውቃላችሁ! የእምነታችንን ምላሽ ማየት ይፈልጋልና። እኛን መፈተሽ ይፈልጋል። ይሄን ታውቃላችሁ? ምላሽህ ምን እንደሚሆን ማየት ይወዳል። "ኦ ጌታ ሆይ፥ አምንሃለሁ። አንተ አዳኜ ነህ። ፈዋሽ አንተ እንደሆንክ አምናለሁ። የመንፈስ ቅዱስ ሰጪ አንተ መሆንህን አምናለሁ። የሚያስፈልጉኝ ሁሉ፥ የምትሰጥ አምላክ አንተ ነህ።" ሰትል፥ ሐጢአቶችህን ሁሉ ተናዘህ ከፈወሰህ በኋላ የምታደርግለትን ለጌታ ቃል ገብተህለት፥ ባለመፈጸሙ ምክንያት፥ እንደ ፈሪ ወደ ሌላ ሁኔታ ከገባህ። እግዚአብሔር ይሄንን አይሰራበትም። አንተን የሚጠቀምበት ምንም መንገድ አይኖረውም። በእምነት ብቻ ሰለሚመልሰ፥ አንተን መልሰ የሚሰጥበት መንገድ የለውም። ከዛ፥ በድንገት፥ ትርቃለህ፥ ሊመልሰልህ አይችልም። እውነተኛ የሆነ እምነት ግን፥ ከእግዚአብሔር

መሆኑ እርግጠኛ በመሆን፥ ባለበት ይጸናል። እርሱ አምላክ እንደሆነ የጸና እምነት ይኑርህ።

47 እግዚአብሔርም ሐጢአቶቻችሁን፥ ወዘተ የመሳሰሉት ነግሮች፥ እንድትናዘዙና፥ እንድታከናውኑ ከጠየቃችሁ፥ እናንተም ከፈጸማችሁት፥ ያኔ እምነታችሁ ጌታ ነው ይላል፥ መፈጸሙም እርግጠኛ ይሆናል። የምትለምኑት ሁሉ ይሆንላችኋል። ኦህ! እንደተረዳችሁት ተስፋ አለኝ - ተስፋ አለኝ። በጌታ እርግጠኞች ከሆናችሁ፥ ጌታም ስለ ቃሉ እርግጠኛ ነው። እናንተን ለመፈተሽ ብቻ ይቆያል እንጂ።

ብዙ ጊዜ እንዲሁ አድርጓል። እስኪ አንድ ወይም ሁለት ነጥቦችን እንመልከት።

48 ለጣኦቱ እንዳይሰግዱ። እግዚአብሔርም የተተማመነባቸው። የዕብራውያን ልጆች እናስታውስ። ወደ እቶኑ እሳት እንደሚጣሉ በሰሙ ጊዜ፥ እንዲህ አሉ፦ “አምላካችን ከዚህ የእቶኑ እሳት ሊያድነን ይችላል። ባያድነን ግን፥ ላቆምከው ምስል አንሰግድም። አሉ።” እያችሁ፥ በእግዚአብሔር እርግጠኛ እና ታማኞች ነበሩ።

49 ያህዌህ እንደሆነ አውቀውታል። ጸሎትን መላሽ እንደሆነ ያውቃሉ። በጉዳያቸው ግን፥ ቢሆንም ባይሆንም፥ ለበጎ ነው ብለው ነበር። ስለዚ አቋማቸውን ገልጸው፥ ሐጢአቶቻቸውን በመናዘዝ፥ ወደ ሞት ተራመዱ።

50 እግዚአብሔር እንዲቃጠሉ ካደረጋቸው፥ ዳግም፥ በትንሳኤ እንደሚያስነሳቸው ታምነው፥ ወደ ጋለው እቶን ሄዱ። በእግዚአብሔር እርግጠኞች ነበሩ፥ ምክንያቱ ጌታ ነገርን ሁሉ ለበጎ እንደሚሰራላቸው አውቀውታልና። እኛም ደግሞ በእግዚአብሔር ከታመንን፥ ጌታ ነገርን ሁሉ ለበጎ እንደሚያደርግልን እናውቃለን።

51 ስለዚህ፥ አንዲት አቋም አደረጉ። ታማኞች ነበሩ፥ በቀጥታም ወደ ጋለው እቶን አመሩ። እምላክም ጸንቶ፥ እየተመለከታቸው፥ በእሳቱ ውስጥ አመላለሳቸው። ምላሻቸውን ለማየት ወዶአልና።

52 ንጉሱ “መለከቱ ሲነፋ ስጋዳችሁን? ” ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ።

“የለም። አልሰገድንም።” ብለው መለሱ። ይሄውና፥ እምነትህ ሲጸና እንዲህ ነው።

“መልካም፥ እንግዲህ፥ ካልሰገዳችሁ፥ አዋጄን አውቃችሁታል? ”

“አዎን፥ አዋጅህን አውቀነዋል።”

“አዋጄ ይህ ነው፥ እቶኑ ከሚግለው ግለት ሰባት እጥፍ እንዲነድ፥ እኔም ወደ እሳቱ እንድወረውራችሁ ነው። አሁን መስገድ ትፈልጋላችሁ? ”

ይሄው እምነታቸው። “የለም። ፈጽመን አንሰግድም።”

53 እግዚአብሔርም፦ “እንግዲህ ምን እንደሚያደርጉ እያለሁ። የእምነታቸው ምላሽ እያለሁ” አለ።

54 ንጉሱም “እጆቻቸውን እሰሩ፥ እግሮቻቸውንም ይታሰር፥ ወደ እቶኑም ውሰዱአቸው።” አለ። እሳቱ በፊታቸው ሆኖ፥ እቶኑ ድረስ ቀረቡ። አሁንም እግዚአብሔር፥ ነገሩን ቆሞ ይመለከታል። እርሱ አምላክ እንደሆነ ግን

እርግጠኞች ነበሩ። ኑዛዜአቸውን ተናዘዋል። የሚያውቁት ነገራቸው ሁሉ፥ ትክክል አድርጓል። እርሱ አምላክ እንደሆነ ታምነዋል።

55 ስለዚ በቀጥታ ወደ ጋለው የእቶን እሳት አመሩ። በመጨረሻዋ ቅጽበት፥ በንፋስ ሰረገላ፥ እየቀዘፈ ከሰማያት መጣ፥ እያጽናናቸውና እየተናገራቸው፥ ትንፋሹን እፍ ብሎ አሰወገደላቸው።

56 አምላክ ሆይ ይህቺ እምነትህ ምላሽ መሰጠት ወደምትችልበት ሁኔታ ትውጣ።

57 የብሉይ ኪዳኑን ኢዮብም፥ ከሳሻችን፥ ሰይጣን፥ ስለ ሰውር ሐጢአቱ፥ በከሰሰው ጊዜ። ኢዮብ ሐጢአት እንዳላደረገ ያውቃል። ያደረገውን ነገር ሁሉ እንደተናዘዘ፣ የሚቃጠል መሰዋዕትም እንዳቀረበ ያውቃል። የእግዚአብሔር ቅድመ ሁኔታም ይህ ነበር። እግዚአብሔር የሚጠብቀው፥ የሚቃጠል መሰዋዕት እና መናዘዝ ብቻ ነበር። ኢዮብም እነኚህን ነገሮች አሟልቶ ነበር።

58 ሰይጣንም፦ “ሀብታም ነውና፥ ግመሎቹን እወስዳለሁ። በጎቹንም ‘እወስድበታለሁ’ አለ” በመጨረሻም የልቡ የሆኑትን፥ ልጆቹን ወሰደበት።

59 እግዚአብሔርን፥ በትክክል ሰለሚያውቅ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግሮ፥ እርሱ እንደሆነ እርግጠኛ ሰለሆነ፥ እንዲሁም ቅድመ ሁኔታዎችን ሰለ አሟላ፥ ኢዮብ፥ የጸና ሆነ። መርምሮ ፈተሸና፦ “የሚቃጠል መሰዋዕቴ ሁሉ አቅርቤአለሁ። በልቤም፦ ‘ምናልባት ልጆቼ ግ-ግ ግብዣ ሲያደርጉ፥ ሴቶች ልጆቼም ባሉበት፥ ምናልባት በልቦቻቸው ሐጢአትን አድርገው ይሆናሉና፥ ሰለእነርሱ እናዘዛለሁ የሚቃጠልም መሰዋዕት እሰዋለሁ’” አልኩኝ።

60 አምላክ ሆይ! አንድ ሰው እግዚአብሔር አድርግ ያለውን ሲፈጽም፥ አምላክ እንደሆነም ሲታመን፥ መመለሱ ግድ ነው። እምነት ሁልጊዜ፥ ወደ ሜዳው ትጠራዋለችና።

61 ቅድመ ሁኔታዎቹን አሟልተህ፥ ትክክል መሆኑን የምታውቀው አድርገህ፣ ተናዘህም ነገሮችን ትክክል ሰታደርግ፣ እንደቀድሞ አድርገህም፥ በእግዚአብሔር ፊት ሰታቀርበው። የፈለገውን ያህል ዝም ቢል አይገደኝም፥ አሁንም አምላክ ነው፥ እምነትን በቦታዋ ለማኖር የሚጠባበቅ አምላክ ነው። እምነታችሁ በሰራችሁ ማየት ፈልጎ ይጠባበቃል፥ ሰራችሁን ሰትፈጽሙ። ምን ምላሽ እንደምትሰጡ ማየት ይፈልጋል።

62 ዘይት ተቀብተህ ከተጸለየልህ፥ እግዚአብሔር ምን እንደምታምን ለማየት ይጠባበቃል። ሌላ ፈዋሽ በከተማው መጥቷል እያሉ፥ ቀጣይ እሁድ መሮጥ፣ ቀጥሎም ያለውን ቀን መሮጥ አይደለም። የእምነታችሁን ምላሽ ለማየት ይጠብቃል። በነጋታው፥ ተመልሳችሁ ፡ “በጣም ሀዘን ተሰምቶኛል፥ የተፈወሰኩ አይመሰለኝም።” እንድትሉ አይደለም። ሲጀምርም፥ ወደ ጸሎቱ ሰልፍ ለመምጣት ብቁ አልነበርክም። አይደለም። አይደለህም። ገና፥ ዝግጁ አይደለህም። አምላክ እንደሆነ አላመንከውም። አይ አይ…

63 ምናልባት፥ “ወንድም ብራንሀም፥ ከአንተ ጋር አልሰማማም።” ልትሉኝ ትችላላችሁ። ድርጊቶቻችሁ ምንነታችሁ ያረጋግጣል። አንድ ሰው ክርሰትያን ነኝ እያለ፥ የሚሰክር፣ የሚያጤስ፣ ቁማርተኛ ከሆነ፥ እንዲሁም ክፉ ቀልዶችን እየተቃለደ፥ “መጽሐፍ ቅዱስ ግማሹ እውነት፥ ግማሹ ግን ሀሰት ነው”

የሚል ከሆነ፥ ወንጌል ሊሰብክ ይችል ይሆናል፥ ገሚሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚክድ ከሆነ ግን፥ አሁንም ድረስ ሐጢአተኛ ሰው ነው። ገና፥ አልተስተካከለም። “በፍሬአቸው ትለዩአቸዋላችሁ።”

64 ጌታ ያው ጌታ እንደሆነ በግልጽ ሰታውጁ፥ ህይወታችሁም በእጁ ሆና፦ “ጌታ ሆይ እኔ አፈር ነኝ አንተም ሸክላ ሰሪ ነህ” ብላችሁ ስታቀርቡለት፥ የምትሹትን ጠይቁት። እምነት ፍጹም አይንገዳገድም። ሳይነቃነቅ ይጸናል።

65 ነገሮች በግራ እና በቀኝ የሚወዳድቁ ቢመስሉም፥ እግዚአብሔር መሆኑን እርግጠኛ ስለሆንክ፥ እምነትህ አትንገዳገድም። እግዚአብሔር ከሆነ፥ የገባውን ቃል መጠበቅ ይኖርበታል። ቃል ገብቶ ቃሉን አያፈርስምና። አምላክ ከሆነ፥ ቃሉን ይጠብቃል። ኦ፥ ይህ ደስ ይለኛል። በቃሉ መጽናት አለበት።

66 ኢዮብ ሁሉንም ነገር አደረገ፥ መስዋዕቱንም አቀረበ። ትክክል መሆኑም ያውቃል። ከዛ በኋላ፥ አንዳንድ የቤተክርስትያን አባላት፥ የሌላ ሐይማኖት ተቋም አባላት መጡና፦ “ኢዮብ፥ ሐጥያተኛ ባትሆን ኖሮ እግዚአብሔር አይቀጣህም፥ ሐጥያተኛ ነኝ ብለህ መናዘዝ ሳይኖርብህ አይቀርም።” አሉት።

67 ኢዮብም ምን ላይ ጸንቶ እንደቆመ ስለሚያውቅ። እንዲህ አለ፦ “ሐጢአቴን ተናዝዣለሁ። የሚቃጠለውን መስዋዕት በእግዚአብሔር ፊት አቅርቤአለሁ፥ ሐጥያተኛም አይደለሁም።” ከዛ በኋላ ኢዮብን ለማውረድ፥ ነገሮች ቀጠሉ፥ ኢዮብ እግዚአብሔርን እና የሚቃጠለውን መስዋዕት እንዲክድ፥ እየቀጠሉ እና እየጨመሩ ሄዱ። አስቀድመህ ባወጅከው ውሳኔ ላይ ሌላ ውሳኔ የወሰንክ ቅጽበት፥ ድክመትህ እና፥ በጌታ ያለህን ጥርጣሬ ያሳያል። ከጌታ አንዳች ነገር ጠይቀህ፥ በጥርጣሬ የምትመላለስ ከሆንክ፥ እማኝ ሳትሆት፥ ተጠራጣሪ ነህ።

68 ኢዮብ የቆመበትን ስለሚያውቅ፥ በቆመበትም መሰረት ጸና።

69 ፐሮኔት፥ በሞሞቻው ሰዓት እንዲህ ማለቱ አይደንቅም፦

> በጠንካራው ዓለት ፡ በክርስቶስ ፡ ቆሜያለሁ፤
> ሌላው ሁሉ ፡ የሚውጥ አሸዋ ነው።

70 በጠንካራው የኢዮብ ውሳኔ፥ ሚስቱ ሳትቀር አፈገፈገች። ጤና በተናጋ ጊዜ፥ አካሉም ሁሉ በእከክ በተወረረ ጊዜ፥ ሰውነቱን እያከከ የተወለደባትን ቀን፦ “ጸሐይ አይብራባት! ጨረቃም በምሽት አትውጣባት።” ብሎ በተራገመ ጊዜ።

ሚስቱ፦ “ኢዮብ ሆይ፥ ግራ ተጋብተሃል። እግዚአብሔርን ረግመህ ለምን አትሞትም? ” አለችው።

71 ቅድመ ሁኔታዎቹንም ሁሉ አሟልቶ ነበርና፤ ከእግዚአብሔር መሆኑ እርግጠኛ ስለ ነበር። ኦ፥ እምነት እምነት አለኝ። እንዲህ አላት፦ “እንደ ሰነፍ ሴት ትናገሪያለሽ።” አላት። ጌታ የሚፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ ሟሟላቱን ያውቅ ነበር፥ ይሄው ነው። እግዚአብሔርም እምነቱን ይፈትሽ ነበር። የእናንተም ይፈትሻል። የእኔምን እንዲሁ ይፈትሻታል።

72 ቅድመ ሁኔታዎቹን ሁሉ ሰናሟላ፦ “ንስሀ ግቡ፥ ሐጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ትቀበላላችሁ።” ተስፋው ይህ ነውና። “ከእናንተ የታመመ ቢኖር፥ የቤተክርስትያን ሽማግሌዎቹን ወደ እርሱ ይጥራ። በጌታም ስም እርሱን ዘይት

ቀብተው፥ ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድነዋል፥ ሐጢአትም ሰርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል።" ይሄው ነው። "ስህተታችሁን፥ ተነጋገሩ፥ አንዳችሁም ለሌላው ጸልዩ።" ያኔ የጌታን ቅድመ ሁኔታ ፈጸማችሁ።

73 "ያመኑትንም፥ እነዚህ ምልክቶች፥ ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋም ይናገራሉ፥ እባቦችን ይይዛሉ፥ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ፥ እነርሱም ይድናሉ።" ይሄው ነው።

74 በእግዚአብሄር ታመኑ። ያመናችሁት እግዚአብሔር ቃል መሆኑን፥ ከልብ እርግጠኞች ሁኑ። ኢዮብ እርግጠኛ ነበርና።

ሚስቱም፦ "ለምን፥ ከግዜ ወደ ጊዜ ትማቅቃለህ። ተራግመህ ለምን አትሞትም? " አለችው።

75 ሰይጣን እንዲህ ያለ ነገር ወደ እናንተ ለመወርወር እንዴት እንደሚወድ። "እየህ፥ በዘይት ከተጸለየልህ በኋላ'ኮ አልተሻለህም። ሰባኪዎቹ ከጸለዩልህ በኋላ'ኮ አልተሻለህም። ሲጀመርም'ኮ፥ ሰባኪዎቹ ትክክል አይደሉም።" የሚቆጠረው፥ በህያው አምላክ ያለህን እምነት እንጂ። ከሰባኪው ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ጉዳዩ፥ ሰባኪው ማን ነው ሳይሆን፤ ጌታ ማነው ነው። ተሰፋ ቃል የሰጠህ ሰባኪው ሳይሆን፥ ቃሉ ከእግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ነው፥ አምላክ በመሆኑ ያለህን እምነት እንጂ፥ የሰባኪው ጉዳይ አይደለም። ስለዚ በእግዚአብሔር ታመን። እግዚአብሔር መሆኑን እና የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ታመን። እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር ነውና።

76 ኢዮብም፦ "አንቺ እንደ ሰነፍ ሴት ትናገሪያለሽ።" "እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔር ነሳ፥ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን።" አላት። በአምላክነቱ እርግጠኛ ነበር።

77 ከአንደበቱ ይህ በተሰማ ጊዜ፥ ነጎድጓድ መጮህ ጀመረ መብረቅም ማብረቅረቅ ጀመረ። እግዚአብሔር ወደ ስራው መጣ። ወደ ስራው ይጠራዋልና። ብዙ ጊዜ ግን ዝም ብሎ ነበር።

78 ይሄን ነው እየሰራ ያለው። እነዚህን ቤተክርስትያን-ሄያጆች፥ ግብዞች የገሀነም-እሰረኛ አሜሪካውያን ተመልከቷቸው። ቁጡ አይደለሁም። አካሄዱ ከአምላክ ጋር ላደረገ ሰው ግን ፡ ሐጢያት ያሰቆጣዋል። አገሪቱ ላይ አልቆጣም፣ ህዝቡ ላይ አልቆጣም፣ ቁጣየ፥ ህዝቡን ለማሳወር እነኚህን ነገሮች ባመቻቸ ዲያብሎስ ላይ ነው።

79 እነኚህ የታወሩ ፓስተሮች እና ሰባኪዎች በሰው-ስራሽ የሰነ መለኮት ነገሮች ተይዘዋል። ዳግም መወለድ አለባችሁ። እግዚአብሔርም ቃሉን ይጠብቃል። እሹሩሩ ሲላቸው ብናይም። አምላክ መሆኑ እርግጠኛ መሆን መልካም ነው። "የአምልኮ መልክ አላቸው፥ ሐይሉን ግን ክደዋልና።"

80 ስለዚህ፥ ያቺ ሚስኪን ሴት፥ ማሰሮው እየጎደለ፣ እየወረደ፣ እየወረደ፣ እየወረደ፣ ነግሮችም ከፊት ይልቅ እየከፉ በሄዱ ጊዜ፥ እግዚአብሔር መሆኑን አውቃለች። እግዚአብሔርም እንዲህ እንዲሆን ያደርግ ነበር። እንዲህ ማድረግ ደስ ያሰኘዋልና። እንዴት ያለ ምላሽ እንደምትሰጡት ለማየት፥ እምነታችሁን መፈተሽ ይወዳል፥ በዘይት ተቀብታችሁ እንዲጸለይላችሁ ያደርጋችሁና፥ ከፊት

ይልቅ እንዲብሰባችሁ አድርጎ፦ “ሰይጣን፥ እንደሚያምነኝ አውቃለሁና፥ ናና ፈትነው” ይለዋል። ጌታን ለዘለአለም ባርኩት! ኡ፡ማይ! [ወንድም ብራንሀም እጆቹን ሁለቴ አጨበጨበ-አርታኢ።] “ቃሌን መቀበሉ አይቻለሁና፥ አሁን ወደ ፈተና አስገባው።” ስለ እናንተስ እንዲህ ይልባችሁ ይሆንን?

81 ስለ ኢዮብ ሲናገር። “የምትፈልገውን ሁሉ አድርግበት፥ እንደሚወደኝ አውቃለሁና፥ ህይወቱን አትውሰድ። የሚቃጠል መሰዋዕቱን አቅርቧልና። ቅድመ ሁኔታዎቹን ሁሉ አሟልቶአልና። አምኖአልና፥ አድርግ ያልኩትን ሁሉ ፈጽሟል። ስለዚህ አሁን፥ ብትፈልግ፥ ከሰል ላይ አንከባልለው።” አለው። የነበረውን ሁሉ ወሰደበት። ጌታ ሲመልስለትም፥ እጥፍ አደረገለት። አዎ፥ ያደርገዋል።

82 አምላክ እንደሆነ በትክክል ማመናችን ለማየት፥ እምነታችንን ይፈትነዋል።

83 ያቺ ምስኪን ሴት፦ “ጸለይኩ። ጸለይኩ። አይገባኝም አሕዛብ እንደሆንኩ አውቄአለሁ።” ማለትዋ፥ አያጠራጥርም።

84 አስታውሱ፥ ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለሷ ተናግሯል። “በኤልያስ ዘመን ብዙ መበለቶች አልነበሩምን? ወደ አንዲቱ ብቻ ተላከ። እርሷም አሕዛብ ነበረች ብሏል።”

85 “ኦ!” “እለምንሻለሁ” አለ። ምናልባት’ኮ፥ የመጨረሻዋን እንጎቻ ባየች ጊዜ፥ በደጅ የነበርው ሞት በር ጥሶ ገብቷል። ትንሽየ፥ አንዲት ጉርሻ፥ ከዛ በኋላ እርሷ እና ልጇ መሞታቸው ነው። ሌሊቱን ሙሉ፥ ሰትጸልይ፥ ትታየኛለች፥ ትኩስ ነፋስ ይነፍሳል፣ ምድርም ተሰነጣጥቃለች፣ ህዝቡም በየጎዳናው ይቆዝማል ያለቅሳል። በቤትዋ ወለል፥ ራመድ ራመድ አለች። ህጻን ልጇን ተመለከተችው። ፕጃማውን ሰታየው፥ እንዳለ ወላልቋል፥ እግሮቹም ተጣብቋል። እጆቿን ስታይ፥ ተሸብሽቧል። ወደፊት ወደ ኋላ ተመላለሰችና፦ “እግዚአብሔር ነው እውቀዋለሁ። ነገሬን ሁሉ ተናዝዣለሁ። የሚጠይቀኝን ሁሉ ፈጽሜያለሁ። ስለ ህይወታችን እለምነዋለሁ፡ ስለ ክብሩ እጠይቀዋለሁ።” አለች። እግዚአብሔርም አያት።

86 ሌሎች ራሳቸውን አሰውበው፥ ዘመናዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ይኑራቸው፥ ትልቅ የዳንኪራ ዳንስ ይኑራቸው፥ ዓለማቸውን ይቀጫሉ። ሴቲቱ ግን ብቻዋን ከእግዚአብሔር ጋር ነበረች።

87 ብርሀን ወገግ ብሏል። እርሷም፦ “ህጻኑ ልጅ ምግብ ፈልጎ ሌሊቱን ሲያለቅስ አድሯል። በአንዲት እፍኝ ዱቄት ምን አረጋለሁ? ” አለች።

88 ታውቃላችሁ፥ ዱቄቱ'ኮ፥ ክርስቶስ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሆነ ሰው ሁሉ፥ የዱቄቱ-ቊርባን ክርስቶስ እንደሆነ ያውቃል። የቊርባን ዱቄት በልዩ ወፍጮ፥ ጥሬው በአንድ አይነት እስኪደቅ ድረስ፥ ይሰለቃል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ስለሆነ። አማኝ ሁሉ ይሄን ያምናል፥ በዚህም ያርፋል። ሃሌሉያ! ያረጀና ቀዝቃዛ ተራ ሐይማኖታችሁን መምረጥ መብታችሁ ነው። ለእኔ ግን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ አምናለሁ። በአክራሪዎች ዓለም መካከልም አቋሜ ይህ ነው። ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ፥ አሁንም አምናለሁ።

89 ወፍጮዎቹ አንድ አይነት አድርገው ያደቁታል፥ እርሱም ያው ነውና። ያኔ የነበረ አምላክ እራሱ ነው፥ በዚህ ማለዳም፥ እርሱ ነው። ለዘለአለምም ያው እንደሆነ ይኖራል። የዱቄቱ ምሳሌ ይህ ነው።

90 በሕዝቅኤል 4 እና፥ ሌሎች እንደምንረዳው፥ ዘይቱ መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው። በዘይት የመቀባታችን ምክንያትም ይህ ነው፥ መንፈስ ነውና። ምንድነው? እንደ ቅዱስ ዮሃንስ 4 "አባት በመንፈስ እና በእውነት የሚያመልኩት እንዲህ ያሉትን ይፈልጋል።" እውነት ኢየሱስ ነው። የዱቄቱ-መስዋዕት እርሱ ነው፥ ዘይቱ ደግሞ መንፈስ ነበር። መንፈሱ፥ ከእውነት ጋር ሲወሃድ የሚወጣው አንዳች ነገር አለ። አንድ ላይ ሲሆኑ፥ እንጀራ ይወጣዋል። ኦ!

91 እምነታችሁ ወዴት አለ? የእግዚአብሔር ቃል፥ በሙሉ ሀይል፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ሆኖ፥ በሞኝነት ሲሰበክ፥ ቃሉ እንደ ዱቄቱ ሲሰበክ፥ ከያዛችሁት ዘይት ጋር ልታዋህህዱት ይገባል። እፍኝ ያህል ጥቂት ይሁን፥ ወይም አንድ ማንኪያ፥ የፈለገ ያህል ይሁን፥ እውነተኛ ነው።

92 መዘጋጀቱ ለምንድነው? የተዘጋጀው ለመስቀል ነው። የተዘጋጀው ስለ ግል-መስዋዕትነት ነው። ማድረግ የሚገባችሁ ይህ ነውና። ቃሉ ሲሰበክ፥ መንፈሱ ኖሮአችሁ አንድ ላይ ስትለውሱት፥ ስቃይን ለመካድ የእራስ-መስዋዕት ነው፣ ህመምን ሁሉ ለመካድ፣ የእግዚአብሔርን ቃል የሚጻረር ነገር ሁሉ፥ ክደን፥ በእርሱ ለመጽናት ነው።

93 ዶክተሩ፥ እንዲህ እንዲያ ነው፥ ወይም ሌላ ይበል፥ ምንም ለውጥ አታሳዩ። በእርሱ ጽኑዎች ሁኑ፥ እግዚአብሔር ተናግሯልና። ዱቄቱ ሲመጣ። ዘይቱ ስላላችሁ። አንድ ላይ ቀላቅሉት።

94 ከማለዳ ብርሃን በኋላ ነግቷል። የሚናገር ድምጽ፥ እንዲህ፦ "ወደ ሜዳው ውጥተሽ ሁለት እንጨቶችን ልቀሚ።" የሚል ድምጽ ይሰማኛል። ቃሉ "ሁለት እንጨቶች" እንድሚል አስተውላቿል? መስቀል'ኮ ነው። ዱቄቱንም ዘይቱንም ይዛለች፥ አሁን ግን ተግባር ለመተግበር፥ በያዘችው ልትሰራ፥ ጥሪ ሊደርሳት ነው። ምንም ያህል ይኑራችሁ፥ የምትፈልጉት ያህል ዱቄት እና ዘይት ቢበዛላችሁም፥ በተግባር መግለጽ ያስፈልጋቿል፥ እራስን-መስዋት ይገባችኋል።

95 ሁለት እንጨቶች። በብሉይ ኪዳን እሳትን የሚያቀጣጥሉበት ከዚህ ሌላ የተሻለ ነገር አልነበራቸውም። እንጨት አምጥታችሁ በሌላ እንጨት ላይ አስደግፋችሁ፥ የሁለቱንም ጫፎች እየፈገፈጋችሁ፥ ከመሀሉ ትለኩሱታላችሁ። ኢንዲያኖቹ እሳታቸውን ይለኩሳሉ። ብዙ ግዜ፥ አቀጣጥያለሁ፥ ሌሊት ሙሉ። ግንድ ብቻ አምጡ፥ ከዛ ይሄኛው በዚህ መልኩ፥ ሌላኛው በዚያ መልኩ፥ ከዛ በኋላ ሲቀጣጠል፥ ወደ እሳቱ ዝም ብላችሁ ግፉት።

96 እንጨቱ መስቀልን ነበር። "ሁለት እንጨቶችን" መጽሀፍ ይናገራል። ድምጹም እንዲህ አለ፦ "ወደ ጓሮው ውጥተሽ ሁለት እንጨቶችን ልቀሚ።" በተመሳሳይ ሰዓት፥ በተራሮቹ ላይ፥ ወደ ነብዩው እየተንጎዳጎደ የወረደ ድምጽ ነበር እንዲህ እያለ፦ "ወደ ከተማ ውረድ። ትእዛዝ አስተላልፌአለሁና" ኦ፥ማይ! ሁለቱ ታዘዙ። ስለዚ አንዳች ነገር ሊሆን ነው። ሁለቱ ታዝዘዋልና።

97 ሰባኪው ቃል ሲሰብክ፥ ተቀባዩ አካል አምኖ ከተገበረው፥ አንዳች ነገር መሆኑ ግድ ነው። በእግዚአብሔር ከታመንን፥ ቃል ገብቶልናልና፥ ሐጢአተኛ ከሆንክ፥ መዳንን ትድናለህ። ከታመምክ፥ ፈውስህን ትፈወሳለህ።

98 እርሱ በእርግጥ አምላክ እንደመሆኑ መጠን፥ ቃሉን ሊጠብቅ ግድ ይለዋል። በትክክል! ሰለዚ ትእዛዙ፦ "መበለት ሴት አዝዣለሁና፥ ወደ ከተማይቱ ውረድ።" ነበር። በነብዩው ፊት ራእይ ተገለጠ። ወዴት እንደሚሄድ እያውቅም፥ እየተራመደ ወጣ። ምንስ ልዩነት ይፈጥራል። ብቻ እሱ ታዟል።

99 እንጨቶቹ ያሉበት ቦታ አታውቅም፥ ሜዳው ላይ በሆነ ቦታ ሁለቱ እንጨቶች አሉ። እናም ወጣች። ዙርያዋን ቃኘች፥ ወደ ሜዳው አቀናች። "አቤት፥ ሙቀቱ!" የከተማው ጫጫታ፥ የሌሊት አድቢ፥ ወይንና እና መጠጥ ጠጥተው፥ እየተንገዳገዱ ያልፋሉ። ወደ መንገድ አየች። ምንም የለም። አንዲት እንጨት አገኘች፥ የመስቀሉ ግማሽ አካል፥ የእራስ-መሰዋዕት። ሌላም እንጨት አገኘች። ሁለተኛውን እንጨት እንዳነሳች...

100 ኦ! እንዴት ያለ ተስፋ አስቆራጭ ነበር ይሆን፥ ሞት በደጅ ቆሞ። እርሷ እና ልጇ አንድ ፍሬ ቁራሽ እንጀራ በልተው ለመሞት ነው። በቃ። አንዳንዴ፥ በጭጋግ መካከል፥ ድምጹን እንሰማለን።

101 ሁለተኛዋን እንጨት ለቅማ መመለስ ስትጀምር፥ ወደ ደጇ የቀረበ ድምጽ መጣ፥ እንዲህ የሚል፥ "የምጠጣውን ውሀ በጽዋ አምጪልኝ።"

102 ዱቄቱ እና ዘይቱ ተለውሶ እና ተዘጋጅቶ፥ ሁለቱ እንጨቶች በእጆቿ እንደያዘች፥ ለማየት ወደ ኋላዋ ዞር አለች። በደንብ ቀምሜዋለሁ፥ ለውሼዋለሁ ብላለች። ቃሉና መንፈሱ፥ እንዲህ መቀላቀል ይኖርበታል። የጸሎትህን ተቃራኒ የሆነውን ነገር ሁሉ ለመገሰጽ እራስህን-መሰዋዕት በምታደርግበት መስቀል ስር መውደቅ ነው። እዎ። "ቀምሜዋለሁ፥ አሁን እንጨቶቹን ላምጣ።"

ድምጽም፦ "የምጠጣውን ውሃ በጽዋ አምጪልኝ" አለ።

103 አየች፥ ደጇን ተደግፎ የቆመ፥ የከሳ-ጉንጭ፥ ጺማም፥ ራስ-በራህ፥ ደጅ ደጇን እያየ፥ በወገቡም ብዙ ዘመን ያሰቆጠረ የበግ ለምድ የለበሰ ሰው፥ አየች። መልኩም እንደው-ጨዋ ሽማግሌ ይመስላል።

104 አለችም፥ "ጌታየ፥ አንዴ ይጠብቁኝ።" እንጨቶቹን በእጇ እንደያዘች፥ ወደ ኋላዋ መዞር ጀመረች። "ውሃየን አካፍለዋለሁ።" የሕይወትን ውሃ፥ ለሰው ሁሉ ለመንገር፥ ወደ ሁሉ ለመሄድ፥ ለማንም ሰው ለመሰጠት ፈቃደኞች ትሆናላችሁ።

105 ድምጹም እንደገና አስተጋባ፦ "የምታካፍይኝ ውሃ ብቻ ሳይሆን፥ በእጅሽም ቁራሽ እንጀራ ይዘሽልኝ ነይ።" የሕይወት እንጀራ፤ የሕይወት ውሃ! የነበረውስ የሕይወት ነውን? እሱ ሲያልቅ በቅርብ ልትጠፋ አይደል። "ውሃሽንም አምጪልኝ፥ እንጀራሽንም አምጪልኝ።"

106 ከዚህ ምን እናገኛለን? ምን እንማርበታለን? "አስቀድማችሁ ጽድቁን ሁሉ እና የእግዚአብሔርን መንግሰት ፈልጉ፥ ሌላው ሁሉ ይጨመርላቿል።"

"ጥቂት ውሃ እና ቁራሽ እንጀራ ይዘሽልኝ ነይ።"

107 ወድያውም፥ ተስፋ ወደ መቁረጥ ተመለሰች። ልክ እንዲህ ስትል እስማታለሁ፦ "ጌታየ፦" "ከሰማኋቸውና፥ ካየኋቸው ሰዎች ሁሉ ትለያለህ።

በምትለው ነገር እጅግ ቅን ትመስላለህ። ይሁን እንጂ፥ እፍኝ ዱቄት እና፥ አንድ ማንኪያ ዘይት፥ ብቻ አለኝ። በእነዚህ ሁለት እንጨቶችም እጋግረዋለሁ። እኔ እና ልጄም፥ እንበላዋለን፥ ይሄን በልተንም እንሞታለን። ያለኝ ይሄ ብቻ ነው።”

108 ቀጥለን የምንሰማው፥ ምንድነው? “አስቀድመሽ፥ ትንሽ እንጎቻ፥ ለእኔ፥ አምጪልኝ።” ማንም ሰው፥ የትኛውም ነገር፥ የወደደውን ይናገር፥ የትኛውም ዓይነት መረጃ፥ ምንም ቢሆን፥ ከሁሉ በፊት፥ ጌታን አስቀድሙ። ከሁሉ በፊት፥ ለእግዚአብሔር። ከሁሉ በፊት፥ ቃሉን።

109 “ዶክተሩ አትድንም ብሎኛል።” ቃሉ ግን፥ ከሁሉ በፊት፥ ነው። “እጅግ ሐጢአተኛ ነኝ። ሴተኛ አዳሪ ነኝ። ቁማርተኛ ነኝ። ሰካራም ነኝ።”

ከሁሉ በፊት፥ የእግዚአብሔር ቃል። “ሐጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን፥ እንደ በረዶ ትነጣለች፥ እንደ ደምም ብትቀላ፥ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።” እግዚአብሔርን፥ አስቀድሙት።

110 “በመጀመርያ፥ ሂጂና፥ ትንሽ እንጀራ አምጪልኝ። ያለሽን ሁሉ፥ ወደ እኔ አምጪው።” ወደ እጆቹ ለማምጣት ፈቃደኞች ናችሁ?

111 ህይወቴን ሙሉ፥ ያለኝን ሁሉ። ሐምሳ አመት ሞልቶኛል። “ዊልያም ብራንሀም፥ ህይወትህን ለእኔ ልታኖራት፥ ፈቃደኛ ነህን? እናንተ ልጆች፥ ህይወታችሁን ለእኔ ለመስጠት፥ ፈቃደኞች ናችሁን?” ፈቃደኞች ናችሁን? የታመማችሁ ሰዎች፥ ትችላላችሁ? ታምኑኛላችሁ? ታስቀድሙኛላችሁ?

112 “ቁራሽ እንጀራ በእጅሽ ይዘሽልኝ ነይ፥ እንዲሁም ጥቂት ውሃ አምጪልኝ።” ተመለከተችው። ይህ ሰው የሚናገረውን የሚያውቅ ሰው መሆኑን የሚነግራት ነገር ነበረ።

ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል። “በጎች... በጎቼ ድምጼን ያውቃሉ።” ቃል ቢሆንም ባይሆንም፥ ትክክል ይሁንም አይሁንም ያውቁታል።

113 ታዘዘችና፥ ዞረች። ማድረግ ያለባችሁም ይህ ነው። ነብዩው አድርጊ ያላትን ለመታዘዝ፥ ፊቷን ባዞረች ቅጽበት፥ ሰው ሁሉ ሊሰማው የሚመኘውን ነጎድጓድ፥ ከሰማያት ወረደ። ሐጢአታኛ ሁሉ እና የታመመ ሰው ሁሉ ሊሰማው የሚመኘውን ፡ “ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላል” የሚል ነጎድጓድ ፡ ከነብዩው ድምጽ መጣ።

114 ይሄን ለመስማት አብዝተን እንናፍቃለን። ሰዎች በቤቴ መግቢያ መንገድ ጠብቀው፦ “ልጄ’ኮ እንዲህ ሆናብኛለች። እጅግ ታማለች፡ የእኔ፡ ህጻን ልጄ። ቃል ብቻ ተናገር።” ይሉኛል። እንደበታችሁ ድረስ ካልመጣ እንዴት ትሉታላችሁ? ከራሳችሁ ትሉት ይሆናል። “ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላል” የምትለዋን ለመስማት ግን፡ ይናፍቃሉ።

115 በመታዘዝዋ ምክንያት፡ ይሄው ወደ እጥሩ ድረስ፡ ቀርቦአል። ጭንጉም ተገፏል። “ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላልና፦ ጌታ በምድር ዝናብ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ፡ ዱቄት ከማድጋ አያልቅም፥ ዘይቱም ከማሰሮው አይጎድልም።” ኦ፥ እንዴት ያለ መጽናናት ነው!

116 እንጎቻውን ሰራች። ለነብዩም ሰጠችው። ተመልሳም በመሄድ ለራሷና ለልጇ አዘጋጀች። በምድር ላይ፡ አብዝተው፡ በሉም ጠጡም።

117 ከወዴት መጣ? እንዴት ገባ? እስኪ በሳይንሳዊ ንግግር ዱቄቱ ከየት እንደመጣ ንገሩኝ። ዘይቱስ ከየት መጣ። ወደ ማሰሮው በየት በኩል ገባ? በየማለዳው እየገለበጠች፥ ምንም እስከማይቀር ድረስ ታፈስዋለች። የዱቄቱ ገንቦንም፡ በየማለዳው እየገለበጠች፥ ትጨርሰዋለች። ተጨማሪ ፈልጋ ስትሄድ ግን፥ ታገኛለች። ታዲያ ከየት መጣ? ፈጣሪ ነውና፤ እግዚአብሔርን በቃሉ ብቻ ያዙት። በእግዚአብሔር ታመኑ።

118 ጤናችሁ ሊታወክባችሁ ይችላል። ሕብረታችሁ ልታጡት ትችላላችሁ። በቃሉ ብቻ ያዙት። እርሱ አምላክ እንደሆነም እርግጠኞች ሁኑ። በቃሉ ብቻ ከያዛችሁት እና አምላክ እንደሆነ ከተማመናችሁበት፥ አሁን የሚታያችሁ ጭጋጋማ ጊዜ ጭጋጉ ላይታይ ይችላል።

119 አንድ ጊዜ፥ በጀርመን አገር፥ ስዕልን አየሁ፥ እስከ አሁን ድረስም በውስጤ ቀርቷል። አንድ ጀርመናዊ ሰዓሊ "የደመና ምድር" የ - የተባለ... ስዕልን ሳለ። በርቀት ስታዩት ከዚህ በፊት አይታችሁ ከምታውቁት ጭጋግ ሁሉ ይልቅ፥ የከፋ-ጭጋግ ነው። ከርቀት ስታዩት፥ እርስ በእርስ የታጨቀ ደመና ነው። ጠጋ ስትሉት ግን፥ ይቀየራል። ክንፎቻቸውን እያጋጩ፥ ለጌታ ሃሌሉያ እያሉ የሚዘምሩ መላእክት ናቸው። ስለዚ አንዳንዴ ጭጋግ እንዲህ ነው። ከርቀት ስታዩት፥ ጭጋጋማና ደብዛዛ ነው። ጌታን በቃሉ ብቻ ግን ያዙት፥ እርሱ አምላክ እንደሆነም ተማምናችሁ፡ ጠጋ በሉት፥ ክንፎቻቸውን-የሚያጋጩ መላእክትን ሆኖው ታገኙታላችሁ።

120 በመጠኑ እንደ አብርሃም ናት፥ የነበራትን ሁሉ እንድትሰጥ፥ በመስውያው እንድታቀርብ የተጠራች። ምናልባት በዚህ ማለዳ፥ እናንተም እንዲሁ እየተጠራችሁ ይሆናል። መንገዳችሁን ተው። አለማመናችሁን አስወግዱ። ያላችሁን ሁሉ እርሱት። ቃሉን እና ዘይቱን ይዛችሁ በአንድነት ለውሱት፥ ራሳችሁን-መሰዋዕት ወደምታደርጉበት መሰውያ አቅርቡት። እኔ በዚህ መድረክ መቆሜ እውነት እንደሆነ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ወደ ሁኔታዎቻችሁ ሲያመጣው፥ ታያላችሁ።

እየጸለይን እሰላሰሉት።

121 ጥያቄ አላችሁ ዛሬ? ከአቅማችሁ በላይ የሆነ ጥያቄ አላችሁ? ይሄው፥ የሆነ ችግር? ኪራይን የምትከፍሉበት ገንዘብ አንሶአቿል? ልጆች አዲስ ጫማ አስፈልጓቸዋል፥ የምትገዙበት ገንዘብ የላችሁም? በቤታችሁ ያለውስ ማድጋ ባዶ ሆኖአልን፥ ማሰሮውስ ደርቋልን? ለከብቶቻችሁ የሚሆን ምግብ መግዛት አትችሉም? ቃል እንደሰጠ፥ አስታውሱ።

122 አምሞሃልን፥ ዶክተሩስ ቀዶ ጥገና ያስፈልግሀል ብሎሃልን? የመክፈል አቅም የለህምን? ጥያቄ አለህን።

123 ሐጢአተኛ ነህን? ዛሬ፥ ጌታ ቢጠራ፥ እንደምትጠፋ እስክታውቅ ድረስ፥ ጥያቄህ ታላቅ ነውን? ከእግዚአብሔር እየሸሸህ ጠፍተሀልን? እንዲሁም የአንድ ቤተክርስትያን አባል ሆነህ፥ ነገር ግን ትክክል አለመሆንህን ታውቃለህን? እንደ ቃሉ መሰረት፥ ትክክል እንዳልሆን ህሊናህ እየነገረህ ነው። የምትጠይቀው ነገር አለህን። እነኚህ ቃላቶች ሁሉ፥ በእሾህማ ስፍራ፥ በአለት ላይ፥ በጠጣር ልብ እንዲወድቁ አታድርጋቸው። በመልካም መሬት፥ ይውደቁ።

124 ታመህ... ዶክተሩም አትፈወስም ቢልህ፥ ጌታን ቀሪ ዘመንህ ሁሉ እንደምታገለግለው ቃል ከገባህለት፥ እርሱ አምላክ እንደሆነም እርግጠኛ ከሆንክ፥ ና ቅድመ ሁኔታዎቹን አሟላ። ጥያቄ ያላችሁ ከሆናችሁ፥ የሆነ ነገር እንደምትፈልጉ፥ አስቀድማችሁ እጆቻችሁን ማንሳት የምትችሉትን ያህል ታወጡለታላችሁን? እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

እንጸልይ።

125 ኦ ጌታ ሆይ፥ አንተ አምላክ ነህና፥ ዛሬ ማለዳ በዚህ ፑልፒት በግልጽ እንደቆምኩ ያህል፥ አንተ ሳታውቃቸው፥ የተነሱ እጆች እንደሌሉ አውቄአለሁ። “ብዙ ድንቢጦች በሁለት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? እናንተም ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ!” ልጅህ ኢየሱስ የሞተላቸውን፥ የእነዚህ ሟች ፍጥረታት እጅስ ምን ያህል አብልጠህ አየህ? ከድንቢጦች ይልቅ እጆቻቸውን ምን ያህል አብልጠህ ታያለህ? እንደማስበው... ደርዘን ድንቢጦች ዛሬ ማለዳ ቢወዳድቁ፥ በአንድ ሳንቲም ባልተሸጡ፥ የሚፈልጋቸው የለምና። እነርሱን ለመቅበር እንቸገር ነበር እንጂ። ይሁን እንጂ እያንዳንዳቸው ታውቃቸዋለህ፥ በአካላቸው ላይ ያለውን ላባ ሁሉ ታውቀዋለህ። የራስ ጸጉራችንም ሁሉ ታውቀዋለህ።

126 ጌታ ሆይ፥ ጸሎትን መልስ። በዚህ ማለዳ፥ አምላክ መሆንህንና፥ መንፈስህ መሆኑን፥ ይተማመኑበት። “እኔ የዚህ እና የዚያ ቤተክርሰያን ነኝ” የሚል የሰለጠነው - ዓለም ሀይማኖታዊ ከንቱነት እና ጭጋግ አራግፍላቸው። አምላክ ሆይ፥ አሁን ከአእምሯቸው ይጥፉ። በዚህች ቅጽበት የዘለአለሙ ህይወት ብልጭታ ይያዙ። ከዛ በኋላ፥ እግዚአብሔር ምን እንደሆነ መፈለግ እና መጠማት ይጀምራሉ፥ እንዲሁም ይተማመኑበታል። ቃሉን ይጠብቃልና።

127 ሐጢአተኛውም፥ ለንስሐ ይቸኩል፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመጠመቅም ዝግጁ ይሁኑ። መንፈስ ቅዱስ እንድትሰጣቸውም ቃል ገብተህልና። ተናግረህልና፥ ጌታ ሆይ። ቃልህን ጠብቅ።

128 በእውነት አምላክ መሆንህን የተጠራጠረ ቢኖር፥ ወደ ኋላ ያፈገፈገ ካለ። እንደተናገርከው “ሐጢአታችሁ እንደ አመዳይ ቢሆን፥ እንደ በረዶ ነጭ ይሆናል፣ እንደ ደምም ቢቀላ፥ እንደ ባዘቶ ነጭ ይሆናል” ብለህልና፥ ዛሬ የተመለሱ ይሁኑ።

129 የታመሙም ቢኖሩ፥ ቃልህን የምትጠብቅ፥ አምላክ መሆንህን ይወቁ። በውስጣቸው ያለውን ዘይት ጋር፥ ማመናቸውን እየተናዘዘ ያለውን መንፈስ ጋር፥ ማንነታቸውን እየሰጡ ባሉበት ቅጽበት። ቃልህን የግድ ትጠብቃለህ። ከቃሉ ጋር፥ የተነገረውን የሀይወት እንጀራ፥ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ ያሳያቸው ዘንድ፥ ከብሉይ ኪዳን እና ከአዲስ ኪዳን፥ መሰረት የተደረገላቸው ክርስቶስን። ቃሉ ከያዙት ከዘይቱ ጋር፥ ከመንፈሱ ጋር ለውሰው፥ በመሰውያው ፊት ቀርበው “ጌታ ሆይ፥ ያለኝ ይሄ ነው፥ ወደ አንተ አመጣሁት” ይበሉ።

ኦ፥ እብዝተህ ታትረፈርፋለህ! የዚህን ታሪክ አምላክ በጉዳያቸውም ላይ ይጠራላቸዋልና! “የሚታዘዘኝ ልጅ አለኝ። በፈተና ውስጥ አሳለፍኩት፥ እንደሚወደኝና፥ እንደሚተማምንብኝ አረጋገጠልኝ። በእኔ ተማምኗልና።” አስብሎ፥ የያህዌን ልብ እንዴት እንደሚቀሰቅስ። “ሳይታክቱ ወደ እግዚአብሔር

የሚቀርቡ ሁሉ፥ የሚሹትንም የሚባርክ አምላክ መሆኑን ሊያምኑ ያስፈልጋቸዋል” ተብሏልና። አንተ ዘንድ ባቀረብንበት በዚህ ሰዓት፥ እርዳን።

130 አሁንም፥ ራሶቻችን ዝቅ እንዳደረግን። እንግዲህ ወደ እርሱ ማቅረብ የምትፈልጉት ነገር ያላችሁ ሰዎች፥ በእግሮቻችሁ ቁሙ፥ እርሱ አምላክ መሆኑን ካልተማመናችሁበት... አምላክ መሆኑ፥ ፈዋሽ መሆኑ፥ ቃሉን እንደሚጠብቅ፣ ወዘተ ከተማመናችሁበት... ጥያቄ ያላችሁ ሁሉ፥ በእግሮቻችሁ ቁሙ። እንዲጸለይለት የምትፈልጉት ሰው ካላችሁ፥ በእግሮቻችሁ ቁሙ። አምላክ መሆኑ እርግጠኞች ከሆ-ከሆናችሁ፥ ጥያቄአችሁን በቅዱሳን ጉባኤ መካከል እንዲታወቅ አድርጉት። ይሄን የምታደርጉት እየ... [በቴፑ ውስጥ ክፍተት አለ-አርታኢ]

“አምላክ መሆኑ አምኛለሁ። ቃሉን እንደሚጠብቅም እርግጠኛ ነኝ። እንዲሁም ጥያቄዎቼ ሁሉ... አሁን፥ ከደሙ ስር እየጣልኩ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ።የምትሉ” ይሄን ካደረጋችሁ፥ ሐጢአት ሁሉ አስወግዱ። ሐጢአት ሁሉ... ማለት አለማመን ነው። የቤተክርስትያን አባል ልትሆኑ ትችላላችሁ፥ ሐጢአት ማለቴ ግን “አለማመናችሁ” ነው። እንደ መስዋዕት አቅርቡት። ወደ መስቀሉ እየቀረባችሁ። ልትሰዉት ነው። አለማመኖቻችሁ ሁሉ፥ አሁን ትሰዉታላችሁ። እርሱ እንደሆነ አውቃቿልና፥ መልስ እንደሚመልስላችሁ እርግጠኞች ናችሁና፥ በእርሱ ላይ ጣሉት። እንዲያ ከሆናችሁ፥ እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሱ። ቀጥሉበትም።

131 ጌታ ሆይ፥ አንተ’ኮ አምላክ ነህ። ይሄው የተቀላቀለ ዘይታቸውና፥ እህላቸው። የጌታ እሳት ወደ ልባቸው በሚወርድበት፥ ወደ መስቀሉ ስር አቅርበውታል፥ (ከልባቸውም ከሆነ) መስዋዕታቸውን ተቀበል። ከሰማይ፥ በእሳት ስረገላ ወርደህ። በጉዳያቸው ላይ ተገለጥ፥ የተደበቀውን ውሃ አመንጭላቸው። እንድትባርካቸውም፥ ሰማይን እና ምድርን ሁሉ ታናውጣለህና።

132 መማናቸውን ለማሳየት፥ እጆቻቸው ወደ ላይ በማድረግ፥ ጥያቄዎቻቸውንና፥ ሁለመናቸውን፥ በመሰውያው ላይ አቅርበው ቆሟልና። የሰማይ እና የምድር አምላክ ሆይ፥ የሰማይ እና የምድር ፈራጅ፥ በእውነት የሰምይ እና የምድር ፈራጅ ጽድቅን ያደርጋል። በእውነት ቃሉን ይጠብቃል፥ አንተ የወንዶቹ ልብ፥ የሴቶቹም ልብ፥ የህዝቡም ልብ የምታውቅ።

133 ጌታ አምላክ፥ እኔም የአገልግሎት ለውጥ እንደሚሆንልኝ ስላወቅኩ፥ እጆቼን ከፍ አድርጌአለሁ። አንተ መሆንህንም አምንሃለሁ። በእሳቱ አምድ ቆመህም አይቼሀለሁ። [ወንድም ብራንሀም ፑልፒቱ ላይ ሶስት ጊዜ በእጁ ደበደበ-አርታኢ።] የሰዎችን ልብ ስትመረምር አይቼሀለሁ። አንድ ቀንም ተሳስተህ አታውቅም። ያኔ፥ እዚህ ከጎዳናው ማዶ፥ ይሄን ስታደርግ፥ እነኚህ ነገሮችን ማድረግ ስትጀምር፥ ቃል ገብተሀል። በዓለም ሁሉ ዙርያ ሁሉም፥ በተደጋጋሚ እና ብዙ ጊዜ ጠብቀሀኛል። አምላክ መሆንህን አረጋግጫለሁ። እርግጠኛ ነኝ።

134 እኔም ከዚህ ህዝብ ጋር አብሬ፥ ጌታ ሆይ፥ ያለኝን ሁሉ መስዋዕት አድርጌ፥ ለአንተ አገልግሎት፥ አቀርባለሁ። ጌታ ሆይ፥ ዳግም በዓለም ዙርያ፥ ለመዞር ጀምሬያለሁ። አምላክ ሆይ አግዘኝ። በየትኛውም ጊዜ አንተን ካላመንኩ፥

ሐጢአቴን ይቅር በለኝ። አለማመኔን ይቅር በል። የሚሹህን የምትባርክ፥ አንተ መሆንህን አውቃለሁና።

135 እንዲሁም፥ እጆቻቸውን አየር ላይ ከፍ አድርገው እንደቆሙ፥ በዚህ ማለዳ፥ የህዝቤን ሐጢአት ድካሞቻቸው እና ጥርጣሬአቸውን ሁሉ እናዘዛለሁ። ጌታ ሆይ፥ ሐጢአታቸውንና ድካማችን ሁሉ እናዘዛለሁ። አንተ አምላክ መሆንህን፥ የሚያረጋግጥ ማህተም ጋር፥ መንፈስ ቅዱስህን ላክልን። እንድትቀበለንና፥ ወደ ክንድህ ልታስገባን፥ እንዲሁም የጠፋብን ሁሉ እንድትዋጅልን፥ አሁን እዚህ ነህ። ጤናችንም ቢሆን፥ መቶ እጥፍ ይመለስልን። ነፍሳችንም ብትሆን፥ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ እንድትችል፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ፥ የፈካችና፥ የምታበራ ዕቃ ሆና ትመለስልን። አለማመንም ከሆነ፥ ተራሮችን የሚያፈልስ እምነት ሆኖ፥ ዳግም ይምጣልን ጌታ ሆይ። ይሁን፥ ጌታ ሆይ።

136 መንፈስ ቅዱስ በህንጻው ውስጥ፥ በህዝቡ ላይና፥ በልቦቻቸው ውስጥ ሞልቶ፥ ህያው የሆነው አምላክ እንዲቀበሉ እየገፋፋቸው እንደሆነ አምነናል፥ እየተዘዋወርክ መሆኑን አምነናል። ይሄን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናደርጋለን።

እምነቴ አንተን ትናፍቃለች,
አንተ የቀራንዮ በግ,
መለኮታዊ መድህን;
ስማጸንህ ስማኝ,
ሐጢአቶቼን ውሰድልኝ,
መቼም እንዳልጠፋ,
ከአንተው ከጎንህ.

137 ከልባችሁ ነው? ተቀበላችሁት? እጆቻችሁ ከፍ አድርጉና “አሁን ተቀብያለሁ። አምነዋለሁ።” በሉ።

በህይወት ጎዳና ስንገዳገድ,
መከራም በዙርያየ ሲከብድ,
እረኛ ሁነኝ,
ጨለማን ገስጸህ ቀን ይሁን በል,
ሀዘንን ጥረግ ፍርሃትን አስወግድ,
መቼም እንዳልጠፋ,
ከአንተው ከጎንህ,

ራሶቻችን ዝቅ እናድርግ።

138 እውነት ሆኖ ሳለ፥ ነገር ግን በማይመች መልኩ ከተሰበከው፥ ከዚህ ጥብቅ፥ ጠንካራ-ቆራጭ፥ ከባድ መልዕክት በኋላ። የጠየቃችሁትን ሁሉ መቀበላችሁን በትህትና ካመናችሁ፥ ከተቀበላችሁት ቅን መንገድ፥ ማንም ሊያስወጣችሁ አትፍቀዱለት። እኔ ምን ያህል ብሰብክ፥ ምንም ያህል ነገር ባደርግ፥ ወይም ሌላ ሰው ምንም ቢያደርግ፥ እንደ ግላችሁ ንብረት አድርጋችሁ እስካልተቀበላችሁት ድረስ ምንም አይጠቅማችሁም።

139 ፍላጎታችሁ ሁሉ፥ ከልባችሁ ካመናችሁ፣ ሐጢአታችሁ ሁሉ ከተናዘዛችሁ፣ ጌታ ይቅር ብሏቿል። በፍጹም እንዳትጠራጠሩ። ከእምነት አፈግፍገህ ከነበርክ፥ በዚህ ማለዳ ተመልሰሀል። መንፈስ ቅዱስ ከሆነ የምትፈልገው፥

ስለ ሐጢአትህ ሰርየት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቅ። የጌታ ቃል ነውና። ስለ ማንም ቤተክርስትያን፥ ስለ ማንም የሀይማኖት ተቋምም ቢሆን ስለ ሌላም ብሎ ቃሉን አያሻሽለውም። እንዲህ መሆኑ ግድ ነው። ቅድመ ሁኔታዋችን ማሟላት ይኖርብናል፥ የቤተክርስትያን ቅድመ ሁኔታዋች ሳይሆን፥ የእርሱ ቅድመ ሁኔታዋች። ማድረግ የሚገባንም ይህ ነው።

140 እርሱ፥ “የእምነት ጸሎት ድውዩን ታድናለች” ብሏል። ታመህም ከሆንክ፥ ስለ ህመምህ የእምነትን ጸሎት ጽልየልሀለሁ። በገዛ ልባችሁ ውስጥ ጸልያችሁታል። እመኑት፥ ተቀበሉት፥ በእርሱ ጸንታችሁ ቁሙ። ምንም ያህል ጭጋጋማ ቢመስልም፥ ሊወስድብኝ የሚችል ነገር አይኖርም። እንዲህ መሆን ይኖርብኛል።

141 “የተሻለኝ አልመሰለም።” ብትሉም፥ ምንም ነገር... እንደው በቃ፥ በአንድነት የተሰበሰቡ የመላእክት ክንፎች ናቸው። ይሄው ነው። ጌታ በበረከት መልኩ ነው። ጭጋጋማ ሊመስልህ ይችላል። ቀረብ ብለህ ግን ተመልከተው፥ ጌታ እግዚአብሔር፥ ቃሉን ጠብቆ ካልቆመ እንደገና እየው።

142 እሁን ራሶቻችን ዝቅ እንዳለ፥ ጉባኤውን ለፓስተራችን፥ ለወንድም ነቪል እሰጣለሁ።

**እግዚአብሔርን ታመን** AMH59-0125

(Be Certain Of God)

ይህ የወንድም ዊሊያም ማርዮን ብራንሃም መልዕክት፥ በጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ U.S.A በሚገኘ በብራንሃም ተበርናክል፥ በጥር 25፥ 1959 እሁድ ጠዋት፥ በኢንግሊዘኛ የተሰበከ መልዕክት ሲሆን፥ ከተቀዳበት የቴፕ ቅጂ፡ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ የታተመ መልዕክት ነው። ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛ ትርጉም በቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግሰ ታትሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org